በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን


# የ1994 በጀት ዓመት
# የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት


አዲስ አበባ

የካቲት 1994

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1994 በጀት ዓመት
## የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
የካቲት 1994

ማ ው ጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| 1. መግቢያ | 1 |
| 2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ | 2 |
| 2.1 የሥነ ሕዝብና ጤና (DHS) በተመለከተ | 2 |
| 2.2 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ የምርምር ውጤቶች ማስታወቂያ ሴሚናር | 3 |
| 2.3 የ1997 ዓ.ም አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅትን በተመለከተ | 3 |
| 2.4 የቫይታል ስታቲስቲክስ በተመለከተ | 4 |
| 2.5 የልጆች የስራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ | 5 |
| 2.6 የማሕበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ | 6 |
| 2.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት | 7 |
| 3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ | 7 |
| 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት | 7 |
| 3.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት | 10 |
| 3.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት | 13 |
| 4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ | 14 |
| 4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ | 14 |
| 4.2 የካርቶግራፊና የመዛግብት አያያዝ በተመለከተ | 15 |
| 5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ | 15 |
| 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና | 16 |
| 6.1 የሰው ኃይሉን በተመለከተ | 16 |
| 6.2 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ | 17 |
| 7. የበጀት አጠቃቀም | 19 |
| ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም | 19 |
| ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም | 20 |
| 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት | 24 |
| 8.1 የዕቃ ግዢን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች | 24 |
| 8.2 ትራንስፖርትና ጥገናን በተመለከተ | 25 |
| 8.3 ሕትመት | 25 |
| 8.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ | 26 |
| 9. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች | 29 |

# የ1994 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የአገሮችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የልማት ፖሊሲዎች እንዲሁም የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችን ለማዘጋጀት የስታቲስቲካዊ መረጃዎች ጠቀሜታ እያደገ መጥቷል:: በመሆኑም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ባለፉት አራት አስርት ዓመታት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ - ነክ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር፣ በመገምገምና በመተንተን ሪፖርት በማዘጋጀት ለመንግሥትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ያሰራጨ ሲሆን፤ አሁንም በማሰራጨት ላይ ይገኛል:: እነዚህን መረጃዎች ለማዘጋጀት ከመንግሥትና ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በርካታ የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሙያ ድጋፍ ለባለሥልጣኑ የተሰጠ ሲሆን፤ የጥናቶቹም ይዘትና የጥራት ደረጃ እያደገ እንዲሄድ ጥረት ተደርጓል::

በ1994 በጀት ዓመት በሁለት ፕሮጀክቶች ስር የሚካሄዱ በርካታ ጥናቶች በባለሥልጣኑ መ/ቤት ለማካሄድ በዕቅድ የተያዘና ሥራቸውም የተጀመረ ሲሆን፤ በተለይም ለአገራችን አዲስና በጣም በርካታ የሰው ኃይል፣ ቁሳቁስና በጀት የተያዘለት የኢትዮጵያ የግብርና ናሙና ቆጠራ ዋነኛው ነው:: በዚህ ቆጠራ በአገሪቱ የሚገኙ ሁሉም ወረዳዎችና በናሙና በተመረጡ ከ12 ሺህ በላይ የቆጠራ ቦታዎች የሚሸፈኑ ሲሆን፤ ከቆጠራው የሚገኘው ውጤትም አስተማማኝና ከዚህ በፊት ከወጡት የግብርና መረጃዎች የተሻለ ሽፋን እንዲኖረው ተደርጎ ተዘጋጅቷል:: በቆጠራው የገጠር፣ የከተማ፣ የሰፋፊና መካከለኛ የንግድና የመንግሥት እርሻዎች እንደዚሁም የአርብቶ አደሩ አካባቢዎችም እንዲሸፈኑ ይደረጋል::

በዚሁ መሠረት የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1994 በጀት ዓመት ለስታቲስቲክስ መረጃ ሃብት መጎልበት አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ አስር ልዩ ልዩ ጥናቶችንና በ1993 ዓ.ም የተጀመሩ ሁለት ጥናቶችን የሪፖርት ዝግጅታቸውን ለማጠናቀቅ እቅዱ በመንቀሣቀስ ላይ ይገኛል:: እነዚህም:-

ሀ. የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣
- የግብርና የገጠር የግል ባለይዞታዎች ቆጠራ (የመኸርና የበልግ፣ የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች ቆጠራ)፣
- የከተማ አካባቢ የግብርና ቆጠራ፣
- የሰፋፊና መካከለኛ የግል፣ የመንግሥትና የማህበራት እርሻዎች ቆጠራ፣ እና
- የአርብቶ አደር አካባቢ የግብርና ቆጠራ ናቸው::

ለ. የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣
- በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የመካከለኛ፣ የትላልቅና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ጥናት፣ እና
- የዋጋዎች ኢንዴክስ ዝግጅት ናቸው::

ሐ. በ1993 ዓ.ም የተጀመሩና በዕቅድ ዓመቱ የሚጠናቀቁ የጥናት ሪፖርቶች

- የመካከለኛ፣ የትላልቅና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ እና
- የሕፃናት ሥራ ሁኔታ ጥናት ( Stand - alone Child Labour Survey)፣ ናቸው::

ከላይ የተጠቀሱት በዕቅድ ዓመቱ የሚጠኑ ጥናቶች ላይ መ/ቤቱ የሚያካሂደው የሥራ እንቅስቃሴ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል ቢሆንም ባለፉት ስድስት ወራት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በዚህ ሪፖርት ተካቷል:: ከዚህም ጋር የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና ሌሎችም አኃዛዊ መግለጫዎች በሪፖርቱ ተጠቃለዋል:: እንደዚሁም ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ በዕቅድ አፈፃፀሙ ላይ የታዩ ችግሮች፣ ለችግሮቹ በመ/ቤቱ የተሰጡ መፍትሄዎችና መ/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት መወጣት ይችል ዘንድ ከበላይ አካል ትኩረት ተሰጥቶአቸው መፍትሄ የሚሹ አጠቃላይ ችግሮች በሪፖርቱ መጨረሻ ክፍል እንዲካተቱ ተደርጓል::

## 2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከሚያካሂዳቸው ጥናቶች ውስጥ የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ የተለያዩ ሕዝብ - ነክ ጥናቶች ዋነኞቹ ሲሆኑ፣ በዘርፉ ያለውን የመረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ ከተካሄዱት ሁለት ብሔራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች በተጨማሪ ሌሎች ጥናቶችንም በማካሄድ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጩ አድርጓል:: በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራትም የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል::

### 2.1 የሥነ - ሕዝብና ጤና ጥናትን (DHS) በተመለከተ

### የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ዋናውን ሪፖርት ለክልሎች ማስተዋወቂያ ሴሚናር ዝግጅት

የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ዋናው ሪፖርት በአገር አቀፍ ደረጃ የአንድ ቀን የማስተዋወቂያ ሴሚናር ቀደም ብሎ መካሄዱ ይታወቃል:: በተመሣሣይ ሁኔታ ይህንኑ

ሪፖርት በሁሉም ክልሎች የማስተዋወቂያ ዓውደ ጥናት ማካሄድ በማስፈለጉ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በትግራይ፣ በድሬዳዋ፣ በሐረሪና በሶማሌ ክልሎች ተካሂዷል:: በቀሪዎቹ ሶስት ክልሎች ማለትም በአፋር፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ ሴሚናሩን ለማካሄድ የዝግጅት ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ:: የማስተዋወቂያ ዓውደ ጥናት በተካሄደባቸው ክልሎች በክልል ደረጃ የተዘጋጁ ሪፖርቶችና የ "power point" ጽሑፎች ተዘጋጅተው ለሴሚናሩ ተካፋዮች የቀረቡ ሲሆን፣ ሴሚናሮቹም የተካሄዱት ከክልሎቹ የሥነ ሕዝብ ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር ነው::

## 2.2 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ የምርምር ውጤቶች ማስተዋወቂያ ሴሚናር፣

መ/ቤቱ ከጣሊያን አገር ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋማትና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሚገኘው የሥነ ሕዝብ ማሠልጠኛ ማዕከል ጋር በመተባበር ሰባት የምርምር ጽሑፎችን ያዘጋጀ ሲሆን፣ ጽሑፎቹን ለሕዝብ ለማስተዋወቅም የአንድ ቀን ሴሚናር በአዲስ አበባ የተባበሩት መንግሥታት የስብሰባ ማዕከል አካሂዷል:: በስብሰባው ከጣሊያን አገር የመጡ ምሁራንና የመ/ቤቱ ባልደረቦች ጽሑፎችን በማቅረብ ተሳትፈዋል:: በሴሚናሩ የተገኙትን አስተያየቶች በማካተት ሰባት ሪፖርቶች ተጠናቀውና በመ/ቤቱ ሕትመት ክፍል ታትመው ለተጠቃሚዎች ተሠራጭተዋል::

## 2.3 የ1997 አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅት

- በ1997 ዓ.ም ሊካሄድ ለታሰበው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል:: አብዛኛው ሥራ በቅድመ ቆጠራ የካርታ ሥራ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በዚህ መጠነ ሰፊ የካርታ ሥራ ወቅት የሚገኘውን መረጃ በስፋት ጥቅም ላይ ለማዋል የካርታ ሥራውን ኮምፒዩተራይዝ ለማድረግ ኮምፒውተሮች፣ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች፣ ዲጂታይዘሮች፣ ስካነሮች፣ ፕሎተሮችና ትላልቅ ከለር ፕሪንተሮች ከውጪ አገር በUNFPA ዕርዳታ ታዘው አብዛኛዎቹን ርክክብ ተፈፅሟል:: በተጨማሪም ለካርታ ሥራው መገዛት ያለባቸው GPS, Plan Printer, Digital area Calculator, Lettering System, Drawing Sets, Drawing Pens, Tracing Paper, ፎቶ ኮፒየሮችና ዲጂታል ኤርያ ካልኩሌተር ከውጪ አገር በUNFPA በኩል እንዲገዙ ተደርጎ ከፊሎቹን ተረክበናል::

- ለካርታ ሥራው የመስክ ሥራና ለዋናው ቆጠራ ጭምር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ዝርዝርና አጠቃላይ የፕሮጀክት ዶክመንት ዝግጅት ከUNFPA CST ከተመደ ባለሙያ ጋር በመተባበር በዝግጅት ላይ ይገኛል፡ ይህ ፕሮጀክት ዶክመንት ለመንግሥትና ለለጋሽ ድርጅቶች ሁሉ እንዲደርስ የሚደረግ ሲሆን፣ ለመንግሥት በሚቀርበው የበጀት ፍላጎትና አጠቃቀም ላይ የሥራውን መርሃ ግብር እንዲያሣይ ተደርጎ ይዘጋጃል።

- የUNFPA አራተኛው ዙር የዕርዳታ ፕሮግራም በ Dec.2001 ስለተጠናቀቀ ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የሚያገለግል የዕርዳታ ፕሮግራም በመዘጋጀት ላይ ሲሆን፣ በቀጣዩ ዙር ፕሮግራም ዝግጅት መ/ቤቱ በአባልነት ተወክሎ በመሣተፍ ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት መ/ቤቱ ለቀጣዩ የ1997 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ አስፈላጊው ዕርዳታ እንዲገኝ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

## 2.4 የቫይታል ስታቲስቲክስ በተመለከተ

- የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲካል የሙከራ የጥናት ቦታዎችን ለመፍጠርም ሆነ ከአስፈፃሚ ተቋማቱ ጋር ለመሥራት የሚያስችሉ የአሠራር ስልቶችን የሚገልጽ " በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም የተዘጋጀ ዕቅድና አፈፃፀም ስልት ረቂቅ" ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም የዚሁ ስታቲስቲክስ የመዝጋቢዎች መመሪያ ሶስተኛ ረቂቅ ለአስተያየት የቀረበ ሲሆን፣ መመሪያው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅጾችን ይዘት፣ የምስክር ወረቀቶችንና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾችን የያዘ ነው።

- ከምዝገባውና ከወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ቅጾች ላይ ሊጠናቀሩ የሚችሉ ዝርዝር የመረጃ ሠንጠረዦች (Proposed List of Tables) በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅተዋል።

- በመ/ቤቱ ለሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኤክስፐርቶችና ቴክኒሽያኖች በተዘጋጁት የመዝጋቢዎች መመሪያ፣ የዕቅድና አፈፃፀም ስልት፣ እንዲሁም ስለ " Civil registration" እና Vital statistics" ጥልቅ ሥልጠናና የመማማሪያ መድረክ በማዘጋጀት ሙያቸውን ለማሻሻል ጥረት የተደረገ ሲሆን፣

መመሪያውንና የአፈፃፀም ስልት ረቂቁን ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትም ለመፈፀም ተችሏል፡፡

- በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን በተመለከተ ቀጣይ ተግባራት በመሠራት ላይ ሲሆኑ፣ ከነዚህም ውስጥ " የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን በማቋቋም የባለቤቶችና ዋነኛ ተባባሪ ድርጅቶች ዋናዋና የተግባር ዘርፎች" በሚል የተዘጋጀው ሁለተኛው ረቂቅ ለአስተያየት ቀርቧል፡፡

## 2.5 የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ

በ1993 ዓ.ም የባለሥልጣን መ/ቤቱን የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ርና የዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) የልጆች የሥራ ሁኔታ ጥናት (Stand Alone Child Labour Survey) እንዲያካሂድ በጠየቀት መሠረት የጥናቱ የመስክ የመረጃ መሰብሰብ ሥራ መከናወኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ጥናት አስመልክቶ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ፦

- የመረጃ ኤዲቲንግና ከዲንግ እንዲሁም መረጃውን ወደ ኮምፒውተር ማስገባት ሥራ ተጠናቋል፣

- መረጃ የማጽዳት (Cleaning) እና መረጃውን በኮምፒውተር ለማጠናቀር የፕሮግራም ዝግጅትና የፕሮሰሲንግ ሥራ ተከናውኗል፣

- ለጥናቱ በተዘጋጀው ማባዣ (raising factor) በመጠቀም የሕዝብ ብዛት የሚያሳዩ ሠንጠረዦች የወጡ ሲሆን፣ ይህንኑ መረጃ ከሌሎች የጥናት ውጤቶች ጋር ለማነፃፀር ተሞክሯል፣

- የጥናቱንም ውጤት ለመተንተን የተለያዩ ሀገሮችን ልምድ ለማግኘት ከአዲስ አበባ የILO መ/ቤት ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ የባለሙያ ድጋፍ በድርጅቱ በኩል እንዲቀርብ በተጠየቀው መሠረት አንድ ኤክስፐርት ከጄኔቫ እንዲመጣ ተደርጎ ከባለሥልጣኑ መ/ቤትና ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በመሆን በጥናቱ ሪፖርት ይዘትና ቅርጽ ላይ ሰፋ ያለ ቴክኒካዊ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

## 2.6 ማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

### ሀ/ የጤና ስታቲስቲክስ

ከአስተዳደር መዛግብት (Administrative Records or Data from Secondary Sources) የሚሰበሰቡ ጤና ነክ መረጃዎችን ከጤና ጥበቃ ሚ/ር እና ከየክልሉ ጤና ቢሮዎች በመሰብሰብ በዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ እንዲወጡ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ሲሆን፣ አብዛኛው መረጃ ተሰብስቦ ከኦሮሚያ፣ ከአዲስ አበባና ከድሬደዋ ጤና ቢሮ መረጃዎችን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።

### ለ/ የትምህርት ስታቲስቲክስ

የ1993 ዓ.ም የትምህርት መረጃ ከትምህርት ሚ/ር ሙሉ በሙሉ የተገኘ ሲሆን፣ ለተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቶ በዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ እንዲወጣ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

### ሐ/ የባህልና ስፖርት ስታቲስቲክስ

የ1993 ስፖርትና ባህል መረጃዎች ከፌዴራል ስፖርት ኮሚሽንና ከባህል ሚኒስቴር የተጠየቀ ሲሆን፣ መረጃዎቹ እንደደረሱ ለተጠቃሚዎች በሚሆን መልኩ አዘጋጅቶ በዓመታዊ መጽሔት ላይ እንዲወጡ ይደረጋል።

### መ/ የሕግና ፍትህ ስታቲስቲክስ

የ1993 የማረሚያ ቤቶችንና የፌዴራል ፖሊስ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሆኑ መጠይቆች ለሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል መ/ቤቶች የተበተኑ ሲሆን፣ ከተበተኑ ቅጾች የተሰበሰበው መረጃ በሚገባ ተጠናቅሮ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል። ከሁለተኛ የመረጃ ምንጭ የሚገኙ መረጃዎችን ይዘት ለማሻሻል መረጃ ሰጪ ከሆኑ መ/ቤቶች ማለትም ከጡረታ ኮሚሽን፣ ከፍትህ ሚ/ር፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከማኅበራት ማደራጃ ጽ/ቤት ከሚገኙ ባለሙያዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እየተሞከረ ነው።

## 2.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

ከተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም ግለሰብ መረጃ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች በመቀበል አስፈላጊውን ስታቲስቲካዊ መረጃና ቴክኒካዊ ድጋፍ አድርጓል።

# 3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

በየዓመቱ በባለሥልጣኑ መ/ቤት እየታተሙ የሚወጡ የሪፖርት ውጤቶች አብዛኛዎቹ የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ዘርፍን የሚመለከቱ ናቸው። በ1994 በጀት ዓመትም በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራምና በግብርና ናሙና ቆጠራ አማካይነት የሚከናወኑ የተለያዩ ጥናቶች በዘርፉ ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ በዕቅድ የተያዙ ሲሆን፣ በዚሁም መሠረት ባለፉት ስድስት ወራት በዘርፉ የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

### 3.1.1 ዓመታዊ የግብርና ናሙና ጥናት

ሀ. የሰብል ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

- በ1994 ዓ.ም ከመስከረም ጀምሮ ለተካሄደው የሰብል ትንበያ ጥናት መረጃ ቅንብር የሚያገለግል የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

- የ1994 ዓ.ም የሰብል ትንበያ ጥናት መረጃ ተቀነባብሮ፣ የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቆና የተገኘው ውጤት ተገምግሞ ሪፖርቱ በሕትመት ላይ ይገኛል።

ለ. የእርሻ መሬት ስፋት መረጃን በተመለከተ

- 1993 የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1993 ዓ.ም በልግ ወቅት የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት መረጃ የኤዲቲንግ ኮዲንግና ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የሪፖርቱ ዝግጅትም በመከናወን ላይ ይገኛል።

- የ1994 ዓ.ም የዋናው መኸር ወቅት የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት መረጃ በመስክ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል።

ሐ. <u>የእርሻ ሥራን /Farm Management Practices/ በተመለከተ</u>

- የ1993 ዓ.ም የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛል።
- የ1994 ዓ.ም የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ በመስክ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል።

መ. <u>መሬት አጠቃቀምን / Land Utilization/ በተመለከተ</u>

- የ1993 የመሬት አጠቃቀም መረጃ ከመስክ ተሰብስቦና ተቀነባብሮ የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት ሪፖርት የተዘጋጀ ሲሆን፣ የመረጃው አስተማማኝነት ግምገማው በግብርና ቆጠራ ሥራ ምክንያት ሊጠናቀቅ አልቻለም።

- የ1994 የመሬት አጠቃቀም መረጃ በመስክ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል።

ሠ. <u>የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ</u>

በ1993 ዓ.ም በየካቲት ወር በተካሄደው የቤት እንስሳት ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም የመረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቋል። የመረጃው አስተማማኝነት ግምገማ ከተከናወነ በኋላ የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቆ ለሕትመት ተልኳል።

## 3.1.2 የ1994 የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራን በተመለከተ

የግብርና ናሙና ቆጠራ በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በመካሄድ ላይ ያለ ሲሆን፣ በመንግስት በኩል ከፍተኛ በጀት ተመድቦለት በመላ አገሪቱ በ464 ወረዳዎች ውስጥ በገጠር በናሙና በተመረጡ 11.264 የቆጠራ ቦታዎች ከ16.000 በላይ የሰው ኃይል በማሰማራት ከመስከረም 2 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ በመስክ መረጃ የመሰብሰብ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል። ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ከተከናወኑ የቆጠራው ዋና ዋና ተግባራት ጥቂቶቹ:-

ሀ. የግብርና ናሙና ቆጠራ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች የሚያከናውኑ ሰባት የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተቋቁመው፣ በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የመጠይቁ፣ የመመሪያና የሌሎች አሠራር መመሪያዎችን ዝግጅት ሥራ በማከናወን በየወቅቱ ለግብርና ናሙና ቆጠራው እንዲውሉ በማድረግ ላይ ሲሆኑ፣ ስለሥራቸውም በየወቅቱ ለግብርና ቆጠራ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባሉ።

ለ. ለግብርና ናሙና ቆጠራ የሚያገለግል የስፋትና የምርት የአካባቢ መለኪያ ኮድ ቡኮች ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ሐ. በግብርና ናሙና ቆጠራ የሚሳተፉ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና በመስክ ለመረጃ መሰብሰቡ ተግባር የሚውሉ የቆጠራ ዶክመንቶችና (መጠይቆችና መመሪያዎች) የመስክ ቁሳቁስ ሥርጭት ዝርዝር በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ኮሚቴዎች ያቀረቡ ሲሆን፣ በዝርዝሩ መሠረትም በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ድርሶ አስፈላጊው መረጃ እየተሰበሰበ ይገኛል።

መ. በግብርና ናሙና ቆጠራ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና በሰብል ትንበያ መረጃ መሰብሰብ ወቅት ከሁሉም የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለቆጠራው አፈፃፀም ተነስተው ለነበሩ በርካታ የቴክኒክና ተዛማጅ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል።

ሠ. ለነባር ስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ስለግብርና ናሙና ቆጠራው አጠቃላይ ይዘትና የቴክኒክ አሠራሩን በተመለከተ የአራት ቀናት ሥልጠና በዋናው መ/ቤት እንዲሰጣቸው ተደርጓል።

ረ. የ1994 ግብርና ናሙና ቆጠራ አካል የሆነው በግብርና የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ወይም ባለይዞታዎች ዲሞግራፊያዊ ባሕሪያት መረጃ የመሰብሰቡ ተግባራት የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በዋናው መ/ቤት የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

3.1.3 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

- በ1994 ዓ.ም በመካሄድ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በተለያዩ ኮሚቴዎች በአባልነት፣ በቆጠራው ለሚሰማሩ መረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች በአሠልጣኝነት እንዲሁም በመስከረም ወር በተካሄደው የሰብል ትንበያ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ላይ በመስክ ሥራ ቁጥጥርና ግምገማ ተሳታፊ ሆነዋል።

- ከተለያዩ ድርጅቶች የሚመጡ የመረጃ ተጠቃሚዎች ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችና የስታቲስቲካዊ መረጃ አጠቃቀም ላይ ተገቢውን የሙያ ድጋፍ አድርገዋል።

- ለመ/ቤቱ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚውሉና ከሌሎች መ/ቤቶች መሰብሰብ ያለባቸው መረጃዎች በአብዛኛው እንዲሰበሰቡ የተደረገ ሲሆን፣ ቀሪዎቹን መረጃዎች በቅርብ በማሰባሰብ ለተጠቃሚዎች በሚሆን መልኩ ተዘጋጅተው ለሚመለከተው ክፍል ይቀርባሉ።

3.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት

3.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክሶችን ሥራ በተመለከተ

ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት

- ከሚያዚያ 1993 እስከ ሰኔ 1993 ዓ.ም ድረስ ያሉት መረጃዎች የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ ለሕትመት በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቷል።

- ከሐምሌ 1993 እስከ ነሐሴ 1993 ዓ.ም ድረስ ያለውን መረጃ የመሰብሰብ ተግባር በኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ ሥልጠና ምክንያት ሳይከናወን ቀርቷል።

- ከመስከረም ወር 1994 ዓ.ም እስከ ኅዳር ወር 1994 ዓ.ም ያሉት መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበው የዳታ ኢንትሪ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፡ የታህሣሥ ወር መረጃ ደግሞ ከመስክ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል፡፡

ለ. <u>በገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

- የሚያዚያ 1993 እስከ ሰኔ 1993 ድረስ ያለው መረጃ የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለሕትመት ተልኳል፡፡

- የገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናት መረጃ ሲሰበሰብ የነበረው የገበያ ቦታዎችን ስርጭት በተከተለ መልኩ ሳይሆን ለግብርና ናሙና ጥናት በሚመረጡ የቆጠራ ቦታዎች ነዋሪ የሆኑ ቤተሰቦች ሚገበያዩባቸው ገበያዎች ላይ ያተኮረ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የገጠሩ የችርቻሮ ዋጋ ጥናት መረጃ አገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ስርዓት አንፃር ሲገመገም ጠቀሜታው የጎላ አልሆነም፡፡ በመሆኑም የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስን ለማስላት የተመረጡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች (Basket of Commodities) በእነዚህ የገጠር ገበያዎች በአብዛኛው አለመገኘት ሳቢያ የገጠር ችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከሐምሌ 1993 ጀምሮ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡

ሐ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

- <u>በ45 ከተሞች የሚካሄደው ነባር የችርቻሮ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ</u>

  ከሚያዝያ ወር 1993 እስከ ሰኔ 1993 ዓ.ም ደረስ ያለው የዋጋ መረጃ ሪፖርት ተጠናቆ ለሕትመት ተልኳል፡፡

- <u>በ106 ከተሞች የሚካሄደው አዲስ የችርቻሮ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ</u>

– በ106 ከተሞች ውስጥ በሚገኙ 119 የገበያ ቦታዎች የሚካሄደው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከሐምሌ ወር 1993 እስከ ጥቅምት ወር 1994 ዓ.ም ያሉት መረጃዎች ተሰብስበው የዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቋል፡፡

የኅዳር ወር 1994 ዓ.ም መረጃ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመከናወን ላይ ሲሆን፡ የታህሣሥ ወር 1994 ዓ.ም መረጃ ከመስከ ተሰብስቦ በመቀነባበር ላይ ይገኛል፡፡

መ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ</u>

- <u>የ 1988 ዓ.ም መሠረት ያደረጉ (ነባር) የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች</u>

ከዚህ ቀደም ሲሠሩ የነበሩ የአገር አቀፍ፣ የገጠርና የከተማ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶችን በተመለከተ እስከ ሰኔ ወር 1993 ዓ.ም. ያሉት ወርሃዊ ኢንዴክሶች ተዘጋጅተውና ታትመው ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ ሲሆን፡ ከሐምሌ ወር 1993 ዓ.ም ጀምሮ የገበያዎች ለውጥ በመደረጉ ከላይ የተጠቀሱት ኢንዴክሶች በአዲሶቹ ለመተካት ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

- <u>የአዲስ አበባ ከተማ ኢንዴክስ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ኢንዴክስ እስከ ኅዳር ወር 1994 ዓ.ም ያሉት መረጃዎች ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ ሲሆን፡ የታህሣሥ ወር 1994 ዓ.ም መረጃ ተቀነባብሮ ለሕትመት ተልኳል፡፡

- <u>የ1993 ዓ.ም መሠረት የሚያደርገው የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ</u>

አዲሱን የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት እንዲቻል በቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ወቅት የተገኘውን የወጪ መጠን የመቶኛ ድርሻ (weight) በመውሰድ የታህሣሥን ወር 1993 ዓ.ም መሠረት አድርጎ ለመሥራት ከለሳው ተጠናቋል፡፡ በመሆኑም ከሐምሌ ወር 1993 ጀምሮ አዲሱን ኢንዴክስ ለእያንዳንዱ ክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ ለመስራት እንዲያስችል ስሌቱ የተከናወነ ሲሆን፡ ለሕትመት በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቶ ለውይይት ለመ/ቤቱ ማኔጅመንት ቀርቧል፡፡

## 3.3 የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት

### 3.3.1 የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ኮንስትራክሽን ስታቲስቲክስ ጥናት

#### ሀ. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት

የ1992 ዓ.ም የዘርፉ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ፣ የኤዲቲንግና ኮዲንግ፣ እንዲሁም የሠንጠረዥ ቅንብር ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

#### ለ. የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃን በሚመለከት፣

የ1992 የዘርፉ መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ በዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መጽሔት ውስጥ ተካትቶ እንዲወጣ ተደርጎ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

#### ሐ. የውጭ የንግድ፣ የትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ መረጃ፣

- እ.አ.አ የ2000ን መረጃ የያዘው የውጪ ንግድ መጽሔት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- እ.አ.አ የ2001 የውጭ ንግድ መረጃ እስከ ሴብተምበር 2001 ድረስ ያለው መረጃ ተሰብስቦ የመረጃ ቅንብርና የእርማት ሥራው በመሠራት ላይ ይገኛል።

#### መ. የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ኢንዴክስ ሥራ

- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የ1992 ዓ.ም መረጃን የሚያካትተው የኢንዴክስ ሥራ የመረጃ ቅንብር ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛል።

- ከዘርፉ ለዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚቀናበሩ መረጃዎች ሥራ አብዛኛው በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

#### ሠ. ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

በሁሉም ዘርፎች እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ለተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠትና አጠቃቀሙን የማስረዳት ሥራ ተከናውኗል።

ሠንጠረዥ 1 **በ1994 የስድስት ወራት የጥናቶች የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1993 በጀት ዓመት መጨረሻ | የ2ኛ ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1 | <u>የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ</u> | | | | | |
| 1.1 | የግብርና ሰብል ትንበያ ጥናት | አዲስ | 15 | 85 | 80 | 94 |
| 1.2 | **የዋናው መኸር ወቅት የግብርና ቆጠራ** | **አዲስ** | **15** | **33** | **32.7** | **99.1** |
| 2. | <u>የዋጋዎች ጥናት</u> | | | | | |
| 2.1 | የ1993 የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር | ነባር | 95 | 5 | 5 | 100 |
| 2.2 | የ1994 የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር | አዲስ | 15 | 40.23 | 40.23 | 100 |
| 2.3 | የ1994 የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከተማ | አዲስ | 15 | 40.23 | 40.23 | 100 |
| 3 | የ1992 የትላል. የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | ነባር | 87.6 | 12.4 | 12.4 | 100 |
| 4 | የ1993 የትላል. የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | አዲስ | - | 11.24 | 11.2 | 100 |
| 5 | የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ጥናት | አዲስ | 10.7 | 29.29 | 3.72 | 12.7 |
| 6. | <u>ዋጋዎች ኢንዴክስ ሥራ</u> | | | | | |
| 6.1 | የአዲስ አበባ የዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 50 | 50 | 100 |
| 6.2 | የአገር አቀፍ የዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 45 | 40.5 | 90 |

## 4. <u>የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ</u>

በየዓመቱ በባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚካሄዱ የተለያዩ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎችና (Methodologies) የአፈፃፀም መመሪያዎችን እንደዚሁም ለጥናቶች የሚያገለግሉ መጠይቆችና ቅጾች ጥራት፣ ብቃትና ወካይነታቸውን በማረጋገጥ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል:: በዚሁ መሠረት በ1994 ዓ.ም የመጀመሪያ ስድስት ወራት የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል::

### 4.1 <u>የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅት</u>

- የ1993 ዓ.ም የልጆች ሥራ ስምሪት ጥናትን አስመልክቶ የማባዣ ሥራ (Raising facror) ተሰርቶና ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል::

- ለግብርና ናሙና ቆጠራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ዶክመንቶችንና ለCrop forecast የሚያስፈልገውን የማባዣ ሥራዎች (raising factor) ተሰርቷል::

- የሰፋፊ/መካከለኛ የግል ንግድ፣ የመንግሥትና የሕብረት ሥራ ማህበራት አርሻዎችን ዝርዝር update ለማድረግ ከዚህ ቀደም የተሰበሰበውን መረጃ በዞንና በወረዳ ደረጃ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

- የግብርና ናሙና ቆጠራ አካል የሆነው የከተማ ግብርና ቆጠራን በተመለከተ መረጃውን በወረዳ ደረጃ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያስችል ዲዛይን ተዘጋጅቶ የመስክ ፍተሻ እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡

- ለአዲቲንግና ኮዲንግ የሚያገለግሉ የአካባቢ መለያ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 4.2 ካርቶግራፊ፣ መዛግብት አያያዝና ስታንደርድስን በተመለከተ

- ለግብርና ቆጠራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ የቆጠራ ቦታና የወረዳ ካርታዎችን ለይቶ በማውጣት አሳትሞ ለሚመለከተው ክፍል በመስጠት በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡

- ከሶማሌና አፋር ክልሎች ውጪ የሚገኙ የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ላይ ለሚካሄደው ቆጠራ የክፍሉ ባለሙያዎች የመስክ ጉብኝት በማድረግ ቆጠራው ስለሚካሄድበት ዘዴና ጊዜ አጥንተው ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርቱን አቅርቧል፡፡

# 5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ እያዘጋጀ የሚያወጣውንና የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ-ነክ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎች ለሚይዘው ለዚህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች የመሰብሰብ ተግባር አብዛኛው ተጠናቆ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በሚሆን መልኩ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ዓመታዊ መጽሔቱ በሚዘጋጅበት ወቅት የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያካትት የሚደረግ ሲሆን እነዚህም፡-

- የሥነ ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድንና ምርት መረጃዎች፣

- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሀገር ሀብት መረጃዎች፣
- የመንግሥት ገንዘብ /Public Finance/ መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የውጭ አገር ንግድ መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና

### 6.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ

በ1994 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,480 ቋሚና 1,665 የኮንትራት በጠቅላላው 3,145 ሠራተኞች ነበሩ ። ከነዚህ ቋሚ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ውስጥ ባለፉት ስድስት ወራት 29 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን የለቀቁ፣ 23 ሠራተኞች በሞት የተለዩ እንደዚሁም 4 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ ሲሆን፣ የ 27 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል። በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ ከነበሩት 1,665 የኮንትራት ሠራተኞች በተጨማሪ 13,300 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 882 ሱፐርቫይዘሮች፣ 185 የዳታ ኢንትሪና የኤዲቲንግ ሠራተኞች 8 ጊዜያዊ የመስክ ሥራ አስተባባሪዎች፣ 241 የአስተዳደርና የሂሳብ ሠራተኞች እንደዚሁም 32 ሹፌሮች በድምሩ 14,648 አዲስ የኮንትራት ሠራተኞች ሲቀጠሩ 175 ሠራተኞች ደግሞ ከሥራ ተሰናብተዋል። በመሆኑም መ/ቤቱ ታህሣሥ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት 17,589 ሲሆን፣ ከእነዚህ ሠራተኞች ውስጥ 1,451 ቋሚና 16,138 ደግሞ ኮንትራት ሠራተኞች ናቸው። በበጀት ዓመቱ ስድስተኛው ወር መጨረሻ ላይ ያለው የመ/ቤቱ ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት በሠንጠረዥ 2 ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ

| ተራ ቁጥር | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቁጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,480 | 1,665 | 3,145 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 27 | 14,648 | 14,675 |
| 3 | በጡረታ የተገለሉ | (4) | - | (4) |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (29) | (175) | (204) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (23) | - | (23) |
| ድምር | | 1,451 | 16,138 | 17,589 |

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 126 ፕሮፌሽናል፣ 919 መለስተኛ ፕሮፌሽናል እና 406 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው:: የእነዚህ ሠራተኞች ብዛት በፆታ ሲለዩ ደግሞ 1,096 ወንዶች /75.5 በመቶ/ ሲሆን 355 ሴቶች /24.5 በመቶ/ ናቸው:: በተመሣሣይ ሁኔታ የኮንትራት ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 64 ፕሮፌሽናል፣ 15,640 መለስተኛ ፕሮፌሽናል እና 434 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ሲሆኑ፣ በፆታ ሲለዩ ደግሞ 12,535 ወንዶች /77.7 በመቶ/ 3,603 ደግሞ ሴቶች /22.3 በመቶ /ናቸው:: ዝርዝሩ በሠንጠረዥ 3 ላይ ቀርቧል::

ሠንጠረዥ 3 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ

| ፆታ | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | |
| ወንድ | 108 | 811 | 177 | 1,096 | 59 | 12,097 | 379 | 12,535 | 13,631 |
| ሴት | 18 | 108 | 229 | 355 | 5 | 3,543 | 55 | 3,603 | 3,958 |
| ድምር | 126 | 919 | 406 | 1,451 | 64 | 15,640 | 434 | 16,138 | 17,589 |

## 6.2 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየጊዜው ለሚያካሂዳቸው ነባርና አዳዲስ ጥናቶች ያለውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ወቅታዊ የሆነ ሥልጠና በመስጠት ሙያቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል:: በመሆኑም በ1994 በጀት ዓመት ስድስት ወራት የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል::

ሀ. በአዲስ መልክ ለተጀመረው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከመላው አገሪቱ ከተመረጡ 119 የገበያ ቦታዎች መረጃ ለሚሰበስቡ ሠልጣኞች ከሰኔ 20 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ሥልጠና በዋናው መ/ቤት የተሰጣቸው ሲሆን፣ ሠልጣኞቹም ወደተመደቡበት የገበያ ቦታ ተሠማርተው ወርሃዊ መረጃ በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ።

ለ. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ በአዲስ አበባ በሁለት ማሰልጠኛ ማዕከላት ከዋናው መ/ቤት፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ከሌሎች መ/ቤቶች ለተውጣጡ 542 ባለሙያዎች ከሰኔ 5 ቀን 1993 እስከ ሰኔ 29 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ የአሠልጣኞች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ በተመሣሣይ ሁኔታ ከሐምሌ 13 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 23 ቀን 1993 ዓ.ም በ47 የተመረጡ የሥልጠና ማዕከላት ለ13,100 የመረጃ ሰብሳቢዎችን ለ2,430 ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና በመስጠት፣ ነሐሴ 24 ቀን 1993 ዓ.ም በማዕከል በተዘጋጀ የመመዘኛ ፈተና ውጤት መሠረት ብቃት ያላቸው ለመስክ ሥራው ተመርጠው በሥራ ላይ ይገኛሉ።

ሐ. በ1993 ዓ.ም ለአንድ ዓመት በጋና ሀገር የማስተርስ ዲግሪ ትምህርት የተከታተሉ ሁለት ባለሙያዎች ትምህርታቸውን ጨረሰው የተመለሱ ሲሆን፣ በተመሳሳይ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከነበሩት መካከል ሦስቱ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደሥራ ተሰማርተዋል። እንዲሁም ሌሎች ሦስት ባለሙያዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ።

መ. በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት የመ/ቤቱን ሠራተኞች የሥራ ብቃት ለማሻሻል በነበረው ዕቅድ መሠረት ሦስት ሠራተኞች ለ5 ቀናት የቢሮ አያያዝ ሥልጠና፣ 2 ሠራተኞች በሰው ኃይል አደረጃጀት፣ 2 ሠራተኞች በዘመናዊ የማኅደር አያያዝ፣ አንድ ሠራተኛ በውስጥ ቁጥጥር እያንዳንዳቸው ለአሥራ ሁለት ቀናት በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት እንዲሰለጥኑ የተደረገ ሲሆን፣ አንድ ሠራተኛ ደግሞ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በሚሰጠው የመካኒክነት ስልጠና ከኅዳር 24/1994 ዓ.ም ጀምሮ የሁለት ወር ስልጠና በመከታተል ላይ ይገኛል።

ሠ. የተሰበሰቡ የግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃዎች ወደ ኮምፒውተር ከመግባታቸው በፊት ለሚከናወን የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ለተቀጠሩ 161 የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሠራተኞች በአጠቃላይ የግብርና ናሙና ቆጠራ መጠይቆች ላይ የ5 ቀናት ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

7. የበጀት አጠቃቀም

ለ1994 በጀት ዓመት ለአጠቃላይ የባለሥልጣኑ መ/ቤት የመደበኛና የካፒታል ወጪ ብር 147,850,200 ከመንግሥት የተፈቀደ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 12,485,500 ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 135,364,700 ተፈቅዷል፡፡ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ 8.45% ለመደበኛ በጀት የተያዘ ሲሆን፣ 91.55% ደግሞ ለካፒታል በጀት የተመደበ ነው፡፡

ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

የተፈቀደው በጀት በሚከተለው የወጪ አርዕስቶች የተከፋፈለ ነው፡፡ ይኸውም:-

- ለደመወዝ ..................ብር 11,130,700.00
- ለውሎ አበል ..............." 40,000.00
- ለሥራ ማስኬጃ ............." 1,314,800.00 የተያዘ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው መጠን:-

- ለደመወዝ ክፍያ ከተፈቀደው 11,130,700 ብር ውስጥ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 4,703,648 ሲሆን፣ ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ከተፈቀደው ብር 4,703,648 (100%) ወጪ ተደርጓል፡፡

- ለውሎ አበል ክፍያ ከተፈቀደው ብር 40,000 ውስጥ ባለፉት ስድስት ወራት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 7,466 ሲሆን፣ ወጪ ከተደረገው ብር 7,664 ብር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህም በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀር (103%) ነው፡፡

- ለሥራ ማስኬጃ ከተፈቀደው 1,314,800 ብር ውስጥ ላለፉት ስድስት ወራት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 160,217 ሲሆን፣ ብር 684,567 በሥራ ላይ ውሏል፡፡ ወጭው በእጅ ከገባው ሊበልጥ የቻለው በ1993 ዓ.ም መ/ቤቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የሚፈለግበትን 1,009,475 ብር የፈሰስ ዕዳ በአንድ ጊዜ እንዲከፍል ተጠይቆ ባለመከፈሉ ለአስፈላጊ ወጭዎች መ/ቤቱ ከሌላ በጀት በመጠቀሙ ነው፡፡

ለ1994 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ ማለትም ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለመደበኛ በጀት በእጅ ገቢ የሆነው ብር 4.871.331 ሲሆን፣ ወጪ የሆነው ደግሞ ብር 5.395.879 ነው። አፈፃፀሙ በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀር 111% ሲሆን፣ ከዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ደግሞ 43% ይሆናል።

ለ. <u>የካፒታል በጀት አጠቃቀም</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1994 ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮግራሞች ብር 135.364.700 የተፈቀደ ሲሆን፣ ይህም ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 3.383.900፣ ለግብርና ናሙና ቆጠራ ፕሮግራም ደግሞ ብር 131.980.800 የተፈቀደ ነው።

ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 1.438.333 (42%) ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ ለግብርና ናሙና ቆጠራ ደግሞ ከተፈቀደው ብር 72.296.778 (55%) ወጪ ሆኖ በሥራ ላይ ውሏል። ለሁለቱ ፕሮግራሞች ከተፈቀደው በጀት ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ በጠቅላላ ወጪ የሆነው ብር 73.735.111 (54%) ነው።

ከተፈቀደው የመደበኛና የካፒታል በጀት በስድስት ወራት ውስጥ ብር 81.760.095 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ የገባ ሲሆን፣ ብር 79.130.990 ደግሞ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። ወጪ የተደረገው በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀርም 96 በመቶ ይሆናል። አሃዛዊ መረጃውም በሚከተሉት ሠንጠረዦች ላይ ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 4/ሀ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የ1994 ዓ.ም

**የስድስት ወራት የመደበኛ በጀት አጠቃቀም**

| የሒሳብ መደብ | ለ1994 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመት ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | | ልዩነት 03 እና 04 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | | 04 | | 05 | |
| 6111 | 10,389,200 | 4.434.209 | 97 | 4.434.209 | 97 | - | |
| 6121 | 118,100 | 3.385 | 20 | 3.385 | 20 | - | |
| 6131 | 623,400 | 266.052 | 60 | 266.052 | 60 | - | |
| 6212 | 126.600 | - | | 125.753 | 15 | -125.753 | 15 |
| 6212 | 105,000 | 8.750 | 00 | 62,494 | 65 | -53.744 | 65 |
| 6214 | 1.000 | - | | | | | |
| 6215 | - | - | | 6.431 | 50 | -6.431 | 50 |
| 6216 | - | - | | 2,264 | 00 | -2.264 | 00 |
| 6217 | 152.600 | 16.955 | 00 | 110.582 | 51 | -93.627 | 51 |
| 6218 | 56,000 | 4.667 | 00 | 13.925 | 36 | -9.258 | 51 |
| 6219 | 10.000 | - | | 726 | 40 | -726 | 40 |
| 6231 | 40.000 | 7.466 | 00 | 7.664 | 94 | -198 | 94 |
| 6232 | 8.300 | 1.455 | 00 | 3.018 | 94 | -1.563 | 94 |
| 6233 | 10.000 | 1.822 | 00 | 9.986 | 00 | -8.164 | 00 |
| 6241 | 102.000 | 18.888 | 00 | 3.442 | 00 | 15.446 | 00 |
| 6243 | 145.100 | 15.035 | 00 | 44.081 | 00 | -29.046 | 00 |
| 6244 | 108.400 | 14.452 | 00 | 80.556 | 12 | -66.104 | 12 |
| 6252 | 28,800 | 7.200 | 00 | 14,400 | 00 | -7.200 | 00 |
| 6253 | 20,000 | 7,850 | 00 | 3,864 | 00 | 3.986 | 00 |
| 6255 | 5,000 | 911 | 00 | 100 | 00 | 811 | 00 |
| 6256 | 35,000 | 6.466 | 00 | 12.794 | 03 | -6.328 | 03 |
| 6257 | 87,300 | 16.189 | 00 | 31.100 | 30 | -14,911 | 30 |
| 6258 | 194.300 | 36.000 | 00 | 86.647 | 68 | -50.647 | 68 |
| 6259 | 19.400 | 3.577 | 00 | 13.271 | 91 | -9.694 | 91 |
| 6314 | 100,000 | - | | 59.127 | 20 | -59.127 | 20 |
| | 12,485,500 | 4,871,330 | 77 | 5,395,879 | 46 | -524.548 | 69 |

ሠንጠረዥ 4/ለ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የስድስት ወር በጀት አፈፃፀም

| የሂሣብ መደብ | ለ1994 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመት ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት 03 እና 04 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 6113 | 827.000 | 333.903 | 421.503 | -87,601 |
| 6114 | 37.700 | 17.600 | 24.234 | -6.634 |
| 6123 | 43.200 | 21,600 | 22.060 | -460 |
| 6212 | 20.000 | 12.500 | 27.316 | -14.816 |
| 6213 | 200.000 | 200.000 | | 200,000 |
| 6217 | 533.000 | 253.174 | 221.200 | 31.974 |
| 6231 | 485.600 | 253.746 | 248.300 | 5.446 |
| 6232 | 70.000 | 34.932 | 8.900 | 26.032 |
| 6241 | 519.200 | 189.800 | 287.200 | -97.400 |
| 6243 | 60.000 | 20.000 | | 20.000 |
| 6252 | 205.000 | 101.050 | 132.870 | -31.820 |
| 6254 | 43.600 | - | | |
| 6257 | 26.400 | 12.000 | 400 | 11.600 |
| 6258 | 200.000 | 99.866 | 31.200 | 68,666 |
| 6259 | 13.200 | 6.000 | 1.000 | 5.000 |
| 6271 | 100.000 | 40.000 | 12.150 | 27.850 |
| | 3.383.900 | 1,596.171 | 1.438,333 | 157,838 |

ሠንጠረዥ 4/ሐ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የማብርና ናሙና ቆጠራ

የስድስት ወር በጀት አጠቃቀም

| የሂሣብ መደብ | ለ1994 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመት ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት 03 እና 04 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 6113 | 48,668,000 | 23,611,179 | 20,314,737 | 3,296,442 |
| 6114 | 12,058,600 | 5,778,079 | 6,082,105 | -304,026 |
| 6123 | 4,366,700 | 1,978,660 | 1,121,837 | 856,823 |
| 6212 | 215,100 | 163,426 | 160,452 | 2,974 |
| 6217 | 6,146,000 | 3,557,120 | 1,901,800 | 1,655,320 |
| 6231 | 46,282,400 | 31,447,190 | 32,639,330 | -1,192,140 |
| 6232 | 1,255,100 | 955,485 | 2,230,262 | -1,274,777 |
| 6241 | 6,200,000 | 4,154,662 | 4,885,382 | -730,720 |
| 6243 | 50,000 | 5,000 | 4,050 | 950 |
| 6252 | 828,000 | 395,520 | 108,455 | 287,065 |
| 6253 | 200,000 | 200,000 | 166,800 | 33,200 |
| 6254 | 4,473,900 | 2,306,472 | 2,271,000 | 35,472 |
| 6255 | 300,000 | 200,000 | 82,700 | 117,300 |
| 6257 | 36,000 | 16,200 | 14,000 | 2,200 |
| 6258 | 720,000 | 360,000 | 183,500 | 176,500 |
| 6259 | 36,000 | 18,000 | 24,668 | -6,668 |
| 6314 | 145,000 | 145,000 | 105,700 | 39,300 |
| | 131,980,800 | 75,291,993 | 72,296,778 | 2,995,215 |

## 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

በባለሥልጣኑ መ/ቤት ያሉት የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ውስጥ በዕቅድ ለተያዙት በሁለት ፕሮጀክቶች ስር ላሉ ጥናቶች እገዛ የሚያደርጉ ሥራዎችን አከናውነዋል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 8.1 የዕቃ ግዥን በተመለከተ

ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት እንዲውሉ ብር 10,612,691.25 ወጪ ተደርጎ የተለያዩ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች እንዲሁም የአገልግሎት ግዢዎች ተፈፅሟል፡፡ ዝርዝሩም በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

በ1994 ስድስት ወራት ውስጥ የተፈፀመ ግዢ

ሠንጠረዥ 5

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት /የአገልግሎቱ ዓይነት | የገንዘብ መጠን ብር | ሣ |
|---|---|---|---|
| 1 | የኮምፒውተር ዕቃዎች፣ ፕሪንተሮችና ተዛማጂ ዕቃዎች | 739.381 | 00 |
| 2 | የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች | 69.482 | 36 |
| 3 | የጽሕፈት መሣሪያ | 775.257 | 84 |
| 4 | ለግብርና ቆጠራ የተገዙ ዕቃዎች(በጥቅል) | 820.490 | 00 |
| 5 | ለግብርና ቆጠራ መጠይቅና ፖስተር የታተመበት | 424.366 | 75 |
| 6 | የተለያዩ የጥገናና የኤሌክትሪክ ዕቃዎች | 56.660 | 52 |
| 7 | በዕርዳታ ለተገኙ ዕቃዎች የቀረጥ፣ ለኪራይና ዲክላራሲዮን | 7.277.008 | 03 |
| 8 | ለማስታወቂያና ለጋዜጦች ግዢ | 15.644 | 40 |
| 9 | ልዩ ልዩ ወጪዎች | 5.512 | 00 |
| 10 | የቆጠራ ዶክመንት ለማጓጓዝ የተከፈለ | 82.709 | 00 |
| 11 | የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች | 160.747 | 40 |
| 12 | ደንብ ልብስና መጋረጃ | 185.431 | 95 |
| | ድምር | 10.612.691 | 25 |

## 8.2 ትራንስፖርትና ጥገና

- በመንግሥት በጀት ለኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የተገዙ 3፫ በUNFPA እና በUSAID ለስነ-ህዝብና ጤና ጥናት 9 የመስክ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በUSAID ለቆጠራ ሥራው በዕርዳታ ከተገዙት 60 ፎርድ ሬንጀር የመስክ ተሽከርካሪዎች ውስጥ ለ59ኙ በድምሩ ለ100 መኪኖች የቴክኒክ ምርመራና ሠሌዳ በማውጣት ለቆጠራው አገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

- 123 የመስክ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎላቸው ለሥራ ተሰማርተዋል፡፡

- 116 የመስክ ተሽከርካሪዎች ከባድና መለስተኛ ጥገናዎች እንዲሁም ሰርቪስ በዋናው መ/ቤት ተደርጎላቸው ለሥራ የተሰማሩ ሲሆን፣ ለእነዚህም ተሽከርካሪዎች በሩብ ዓመቱ በጠቅላላው ብር 2,398,685 ወጪ ሆኗል፡፡

- 17 የመስክ ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን ስለነበራቸው ተጠግነው ወደ ሥራ የተሰማሩ ሲሆን፣ ሌሎች 6 ተሽከርካሪዎች በጋራዥ ጥገና ላይ ይገኛሉ፡፡

- 34 የመስክ ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ ብልሽት ምክንያት በአገር ውስጥ መለዋወጫ ዕቃቸው ባለመገኘቱና የመጠገኛ ዋጋቸውም ከፍተኛ በመሆኑ ያለአገልግሎት ቆመዋል፡፡

- የባለሥልጣን መ/ቤቱ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለተሽከርካሪዎች በጠቅላላው ብር 122,884 ለነዳጅና ቅባት ወጪ ተደርጓል፡፡

## 8.3 የሕትመት ዋና ክፍል

የመ/ቤቱ የሕትመት ዋና ክፍል ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ታህሣስ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 36,986 የተለያዩ ዓይነት ጥራዞች፣ 16,113,428 ገጽ ያላቸው ሕትመቶች አትሞ ለሚመለከተው ክፍል ያቀረበ ሲሆን፣ ከተለያዩ ክፍሎች ለሚቀርቡለት የፎቶኮፒ አገልግሎት ሰጥቷል፡

8.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

ሀ. በማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት

- ለኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የተዘጋጁ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች ማለትም በራሪ ጽሑፎች፣ ፖስተሮች፣ መፈክሮች፣ መዝሙርና የቪዲዮ ክር ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለመገናኛ ብዙሃን (ለኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት) እንዲደርስ በማድረግ ለቅስቀሳ ተግባር እንዲውሉ ተደርጓል፡

- ለግብርና ናሙና ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ከተመረጡት ድራማዎች "ናሙና" የተሰኘው ድራማ ለቴሌቪዥንና ለሬዲዮ ስርጭት በሚያመች መልኩ እንዲዘጋጅ የተደረገ ሲሆን፡ አጠቃላይ ሥራው በመ/ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ ለመጨረሻ ግምገማ ቀርቧል።

- ስለግብርና ናሙና ቆጠራው ዓላማ፣ ይዘት፣ አጀማመር... ወዘተ በተመለከተ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊዎች መግለጫዎችን በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ተችሏል፡

- በባለሥልጣኑ መ/ቤት የተዘጋጁ 2,531 ሪፖርቶች ለ274 መ/ቤቶችና መረጃ ተጠቃሚዎች በነፃ እንዲሰራጩ የተደረገ ሲሆን፡ 1,620 ሪፖርቶች ደግሞ በብር 45,232.20 ሺያጭ ተፈጽሟል። በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት በጠቅላላው 4,151 ሪፖርቶች ስርጭት ተካሂዷል፡

- ባለፉት ስድስት ወራት በአገልግሎቱ የመ/ቤቱ የስልክ ማውጫና የ1994 የቀን መቁጠሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን፡ የመ/ቤቱ ብሮሸር ተዘጋጅቶ ለሕትመት ተዘጋጅቷል፡

- የመ/ቤቱ ቤተ መፃሕፍት ከውጭና ከመ/ቤቱ ለመጡ ተጠቃሚዎች አገልግሎት የሰጠ ሲሆን፡ በተመሳሳይ ከውጭና ከአገር ውስጥ ለመጡና መረጃ ለሚፈልጉ እንግዶች አስፈላጊው መረጃ የተሰጠ ሲሆን፡ የመ/ቤቱን ቤተመጻሕፍት የብሪቲሽ ካውንስል ቤተመፃሕፍት አባል በማድረግ የመ/ቤቱን ሠራተኞች የተሻለ ግልጋሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። በተጨማሪም

የቤተመፃሕፍትና ዶክመንቴሽን አገልግሎት የተጠቃሚዎች ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ ማኔጅመንት ለውሣኔ ቀርቧል።

ለ. <u>የሥራ አመራርና ሥልጠና አገልግሎት</u>

- ለግብርና ቆጠራ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ለማሟላት ከ16,000 በላይ በተለያዩ የሥራ መስክ ላይ የሚሳተፉ የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር አስፈላጊው ፎርማሊቲ በማዘጋጀት ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተልኮ፣ ኮሚሽኑም የቀረበለትን ዶክመንት ከመረመረ በኋላ የተጠየቀው የሰው ኃይል ቅጥር እንዲፈፀም በመፍቀዱ የአብዛኛው ቅጥር ተፈጽሟል፡

- የመ/ቤቱ የሥራ ሽፋን በየጊዜው እያደገ በመምጣቱ ምክንያት ተጨማሪ የሰው ኃይል በቋሚነት እንዲቀጠር ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የቀረበው የ195 የሥራ መደብ ጥያቄ መፈቀዱ ይታወቃል። ይህም የተፈቀደው የሰው ኃይል የሥራ ዝርዝር ተዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ ተልኮና ምደባው ተሠርቶ የደረሰን ሲሆን፣ የተፈቀደውን የሰው ኃይል በቅጥርና በውስጥ ዕድገት የማሟላት ሂደት በሚቀጥለው በጀት ዓመት ይከናወናል።

- የመ/ቤቱ የሥራ ሽፋን በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል። በመሆኑም ለአንዳንድ መምሪያዎችና አገልግሎቶች የተፈቀደው የሰው ኃይል አሁን ከሚሰራው ሥራ አንፃር ሲታይ በቂ አይደለም። ይህ ችግር ጎልቶ ከታየባቸው ውስጥ የሕግ አገልግሎት አንዱ ሲሆን፣ አገልግሎቱ ባለው የሰው ኃይል በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የሚነሱ የሕግ ጉዳዮችን ለመከታተል አስቸጋሪ ሆኗል። ይህን ችግር ለመቅረፍ ተጨማሪ የሦስት ነገረፈጅ የሥራ መደብ እንዲፈቀድ ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጥያቄ ቀርቦ ምላሹ እየተጠበቀ ይገኛል፡

ሐ. <u>የሕግ አገልግሎት</u>

- የመ/ቤቱ ባልደረቦች በነበሩበት ጊዜ የተሰጣቸውን የመንግሥት ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው በጠቅላላው ብር 43,710.01 ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ በሚመለከተው ፍርድ ቤት በኩል ስለተወሰነ ስለ አፈፃፀሙ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡

- በተመሣሣይ ከሌሎች የመ/ቤቱ ሠራተኞች መ/ቤቱ የሚፈልግባቸውን በጠቅላላው ብር 59,745.55 ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት መ/ቤቱ ክስ መስርቶ ጉዳዩን በመከታተል ላይ ይገኛል፡

- የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች በተለያዩ ጊዜያት በሰዎች ላይ ላደረሱት አደጋ እንዲከፈላቸው የጠየቁት የጉዳት ካሳ በጠቅላላው ብር 302,840 በሚመለከተው ፍርድ ቤት በኩል እየታየ ይገኛል።

መ. <u>የኦዲት አገልግሎት</u>

- አገልግሎቱ የዋናው መ/ቤትንና የ47 ቱን ቅ/ጽ/ቤቶች የሚንቀሳቀሰውን በርካታ የገንዘብ ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት ሂሳቡን በቅድሚያ እየመረመረ አስፈላጊውን ማጣራት እያከናወነ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ ያደርጋል። በዚሁ መሠረት ባለፉት ስድስት ወራት ለዋናው መ/ቤትና ለ47ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 73,482,786 ቅድመ ምርመራ አድርጓል፣ እንደዚሁም 40,704,797 ወጪዎችን ዝርዝር ምርመራ አካሂዶ፣ ሂሳቡ እንዲወራረድ ተድርጓል፡

- በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ፕሮጀክቶች ለየቅ/ጽ/ቤቶቹ ገንዘብ በባንክ በኩል ሲላክ እና የተለያዩ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች የገንዘብ ጥያቄ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ቅድመ ምርመራ ተድርጓል፡

- ለመ/ቤቱ አገልግሎት የሚሰጡ የመስክ ተሽከርካሪዎችን የነዳጅ አጠቃቀም በተመለከተ የነዳጅ ደረሰኝ ወጪ፣ በመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ መሞላቱንና ተሽከርካሪዎች በሊትር ምን ያህል ኪሎሜትር እንደተጓዙ ቁጥጥር ተድርጓል፡

- የመንግሥት ገንዘብ በግለሰቦች እጅ ገብቶ ባለመመለሱ ምክንያት ጉዳዩ በፍርድ ቤት ደረጃ ሲታይ ለሚቀርቡ የኦዲት ሪፖርት ለማቅረብ አስፈላጊውን የሂሣብ ምርመራ በማካሄድ ለጠየቀው ፍ/ቤት አፋጣኝ ምላሽ ተሰጥቷል፡

- በተጨማሪ የሰባት ቅ/ጽ/ቤቶችን ገንዘብ ያዥና የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኞችን ርክክብ ተፈፅሟል።

ሠ. <u>የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት</u>

- መ/ቤቱ በ1994 በጀት ዓመት ሊያካሂዳቸው በዕቅድ የተያዙ የሁለት ፕሮጀክቶች (የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይና የግብርና ናሙና ቆጠራ) በጀት ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎት ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መርሃ ግብሩ መሠረት ወርሃዊ የገንዘብ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል፡

- የመ/ቤቱን ወርሃዊና የሩብ ዓመት የፕሮጀክቶች የፊዚካልና ፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል ተላልፏል፡

- ለ1995-97 የመ/ቤቱን የኢንቨስትመንት ፕሮግራም ከባለሥልጣኑ የስታቲስቲክስ ጥናት ቅደም ተከተል በመነሳት የበጀት ፍላጎቱን ለሚመለከተው አካል እንዲተላለፍ ተደርጓል፡

## 9. <u>በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች</u>

ሀ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት በበጀት ዓመቱ በመላው አገሪቱ የጀመረው የግብርና ናሙና ቆጠራ ተግባር ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል በመጠየቁ በተለይም ለመስክ ሠራተኞች ትኩረት በመስጠት ከአጎራባች ክልሎችና ዞኖች ለመቅጠር ተሞክሯል። ሆኖም መ/ቤቱ የቆጠራ ሥራውን ለማቃናት ቀድሞ ከነበሩት 22 ቅ/ጽ/ቤቶች በተጨማሪ 25 ጽ/ቤቶች ከፍቶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ ለእነዚህና ለቀድሞዎቹ ጽ/ቤቶች የድጋፍ ሰጪ (የአስተዳደርና የፋይናንስ ሥራ) ሠራተኞችን ለመቅጠር ተሞክሮ እስከ አሁን ለማሟላት አልተቻለም። በመሆኑም ጽ/ቤቶቹ ባልተሟላ የሰው ኃይል እየተንቀሳቀሱ ሲሆን፣ የቴክኒኩን ሥራ እንዲያስተባብሩ የተመደቡ ባለሙያዎች የአስተዳደሩን ሥራ ደርበው እንዲሰሩ በመደረጉ አስፈላጊ ያልሆነ የሥራ ጫና ፈጥሯል፡

ለ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሥራ ስፋት በየዓመቱ እየጨመረ በመሄዱ በርካታ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ቀጥሮ በማሠራት ላይ ይገኛል። በየጊዜው በሚቀርበው የባለሥልጣኑ መ/ቤት ሪፖርቶችና የበጀት ፍላጎት ጥያቄ ላይ አሁን ካሉት ቢሮዎች በተጨማሪ በዛ ያሉ ክፍሎች

የሚኖሩት ቢሮ እንዲያገኝ ወይም በግንባታ እንዲያሟላ ሲጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ባለመሆኑ በከፍተኛ የሃገር ሀብት የተማሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ተስማሚ የሆነ የሥራ ቦታ ባለማግኘታቸው የዕለት ተዕለት ሥራቸውን በማከናወን ረገድ ችግር ተፈጥሯል:: እንደዚሁም በተለያዩ ጥናቶች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በቂ ቢሮዎችና መጋዘኖች ቢያስፈልጋቸውም ማሟላት አልተቻለም፡ ስለሆነም ይህ የቢሮና የቦታ ጥበት ዘላቂ መፍትሄ እንዲሰጥበት ያስፈልጋል፡

ሐ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚያካሂዳቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ ነክ ጥናቶች ከፍተኛ የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚጠይቁ በመሆናቸው መ/ቤቱ በየጊዜው ያሉትን ባለሙያዎች ለከፍተኛ ትምህርትና የተለያዩ ዓለማቀፋዊ ሴሚናሮች፣ አውደ ጥናቶችና የምርምር ሪፖርቶች በሚቀርቡበት ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ በማድረግ ያላቸው ልምድ የሚያካፍሉበትንና ተጨማሪ ተሞክሮዎች የሚያገኙበትን ሁኔታ እያመቻቸላቸው ይገኛል:: ሆኖም ለእነዚህ ባለሙያዎች አሁን የሚከፈላቸው ደመወዝ በተመሳሳይ ደረጃና ሙያ ካላቸው ሌሎች ድርጅቶች ከሚሠሩ ባለሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ለተሻለ ክፍያ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎቹ መ/ቤቱን እየለቀቁ ይገኛሉ:: ስለዚህ መንግስት ይህንን ችግር ለዘለቄታው መፍታት እንዲቻል ለመ/ቤቱ ልዩ የደመወዝ ስኬል እንዲፈቀድ እንጠይቃለን፡

መ. በባለሥልጣኑ መ/ቤት አሁን ባለው አወቃቀር በተወሰኑ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ላይ አስፈላጊ ያልሆነ የሥራ ጫና የተፈጠረ በመሆኑ በተለይም 22 ቅ/ጽ/ቤቶች በአንድ መምሪያ ከዋናው መ/ቤት ለመቆጣጠርና ለመምራት አስቸጋሪ ስለሚሆን፣ ሌሎች ቴክኒካል መምሪያዎችንና አገልግሎቶችን ከ22ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር መምራት የሚችል በም/ዋና ሥራ አስኪያጅ ደረጃ መ/ቤቱ በተጨማሪ ቢዋቀር የተሻለ እንደሚሆን ተገንዝበናል:: ስለዚህ የመ/ቤቱን መዋቅር በአዲስ መልክ ለመለወጥ እንዲቻል በባለሙያዎች የሚጠናበት ሁኔታ በመንግሥት እንዲመቻች ወይም ከዚህ በፊት መ/ቤቱ የነበረው መዋቅር መሻሻል ተደርጎበት እንደገና በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እንጠይቃለን፡